# የሐዋርያት ሥራ መጽሀፍ ጥናት

በዴንቨር ኮሎራዶ፡ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ

ዲሴምበር 2015

**አርዕስት** **ማውጫ** **ገፅ**

**መግቢያ ....................................................................................................3**
**ጥናት 1 የኢየሱስ ወደ ሰማይ ማረግ ....................................................................4**
**ጥናት 2 የማትያስ መመረጥ ..............................................................................5**
**ጥናት 3 የመንፈስ ቅዱስ መውረድ .......................................................................6**
**ጥናት 4 የጴጥሮስ ስብከት ...............................................................................7**
**ጥናት 5 የአማኞች የህብረት ኑሮ .......................................................................8**
**ጥናት 6 የሽባው ሰው መፈወስና የጴጥሮስ ስብከት ..................................................9**
**ጥናት 7 ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ....................................................10**
**ጥናት 8 የአማኞች ጸሎትና ማህበራዊ አኗኗር .......................................................11**
**ጥናት 9 ሐናንያና ሰጲራ ..............................................................................12**
**ጥናት 10 የሐዋርያት አገልግሎትና መከራን መቀበል...............................................13**
**ጥናት 11 የሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ .................................................................14**
**ጥናት 12 የእስጢፋኖስ መያዝ .........................................................................15**
**ጥናት 13 እስጢፋኖስ በሸንጎው ፊት ያደረገው ንግግር እና መወገር .............................16**
**ጥናት 14 የፊልጶስ አገልግሎትና ጠንቋዩ ሲሞን ......................................................17**
**ጥናት 15 ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ .........................................................18**
**ጥናት 16 የሳውል ማመን ...............................................................................19**
**ጥናት 17 ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም ............................................................20**
**ጥናት 18 የጴጥሮስ አገልግሎት በልዳን የኢዮጴ ......................................................21**
**ጥናት 19 የቆርኔሌዎስና የጴጥሮስ ራእይ ............................................................22**
**ጥናት 20 ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ...................................................................23**
**ጥናት 21 ጴጥሮስ አህዛብ ቤት ለምን እንደገባ አስረዳ ...........................................24**
**ጥናት 22 የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ...................................................................25**
**ጥናት 23 የያዕቆብ መሰዋትና የጴጥሮስ ከእስር መውጣት ..........................................26**
**ጥናት 24 የሄሮድስ አሟሟት ............................................................................27**
**ጥናት 25 የበርናባስና የሳውል(የጳውሎስ) መላክ .....................................................28**
**ጥናት 26 የበርናባስና የጳውሎስ አገልግሎት በጲስድያ ...............................................29**

መግቢያ

የሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ከየኢሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ ሐዋርያቶች (የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት) የመንፈስ ቅዱስን ሃይል በመቀበል ስለ ክርስቶስ መመስከርና ወንጌልን በመስበክ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በይሁዳ በሰማርያና በአህዛብም መካከል ቤተ ክርስቲያንን በመትከል ደቀ መዛሙርት ያፈሩበትን ገድል (ታሪክ) የሚገልጽ መጽሃፍ ነው።

የሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ጸሃፊ ስም በሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ውስጥ ባይገለጽም «ኢየሱስ ...ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ መጀመረይውን ነገር ጻፍሁ»፤ ብሎ ጸሃፊው መግለጹ የሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ የሌላ መጽሃፍ ቅጥያ መሆኑን ያሳያል። ለቴዎፍሎስ የተጻፈው ሌላኛው መጽሃፍ የሉቃስ ወንጌል በመሆኑ ይኸው ጸሃፊ ነው የሐዋርያትን ስራ የጻፈው የሚል ግምት ያሳድራል ። የቤተ ክርስቲያንም ታሪክ የሁለቱ መጽሃፍ ጸሃፊ ሉቃስ መሆኑን ይናገራል ። ሉቃስ የወንጌሉን የመስፋፋት ታሪክ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ ሰምቶ የጻፈ ብቻ ሳይሆን እርሱም በታሪክ ውስጥ የተካፈለ ነበር ። በየሐዋርያት ሥራ አንዳንድ ክፍሎች ላይ «እኛ» «ሁላችንም» የሚሉ ቃላቶችን ይጠቀማል ። ይህም ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር አብሮ ተጓዥ መሆኑን ያሳየናል። ሐዋ 16፤10-17 ፣ 20፤5-6 ፣ 21፤18 ፣ 27፤ 1 እና 28፤16 መመልከት ያስፋልጋል ።

የሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ የተጻፈበት ጊዜ በመጽሃፉ ውሰጥ ባይጠቀስም ፤ ነገር ግን በመጽሃፉ ውስጥ ከተጠቀሱት የታሪክ ክንዋኔዎች በመነሳት አማካይ የሆነ ጊዜ ልንሰጥ እንችላለን። በሐዋርያት ስራ ላይ የተፈጽሙት ክንዋኔዎች የተጠናቀቁት ወደ 60 ዓ.ም ገደማ ነው። ሉቃስ ሐዋርያው ጳውሎስ በ59 -60 ዓ. ም ገደማ ወደ ሮም ሲሄድ አብሮት ነበር ። (ሐዋ 13፤20) በመጽሃፉ ውስጥ በተጠቀሱና ባልተጠቀሱ ክንዋኔዎች ላይ በመመርኮዝ መጽሃፉ የተጻፈበት ዘመን ከ60 – 63 ዓ. ም አካባቢ ባለው ጊዜ ያደርጉታል ።

የሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ የመጻፉ ምክንያት በኢየሱስ ሐዋርያነት ላይ በኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ ሃይል መውረድ በአይሁድ ዘንድ የተጀመረችው ቤተ ክርስቲያን በዚያው የመንፈስ ቅዱስ ሐይል ተግዳሮትን ሁሉ በመቋቋም ወደ አህዛብ በአሸናፊነትና በደስታ መዝለቋን በዚህም ሂደት የሰዎች ህይወት መለወጡንና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በመመልከት የቤተ ክርስቲያን ቀጣይ አገልግሎት የእግዚአብሔር ዓላማ እንደሆነ እንድናጤን በመፈለጉ የመነጨ ይመስላል ።

የሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ዋንኛ ትምህርቶች

1. ጸ**ሎት** ፡- በሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ጸሎት በቤ/ክ ውስጥ ቁልፍ የሆነ ቦታ ተሰጥቶት እንደነበር ያሳየናል። ሐዋ 1፣ 14 ፣ 24 2 ፣ 42 4፣ 31
2. **ምስክርነት** ፡- የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሰጠው የመጨረሻ ትእዛዝ ምስክሮቼ ሁኑ የሚል ነው ። የጥንት ክርስቲያኖች ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች ለመሆን ምንም አይፈሩም ነበር። 5 ፣ 29 7፣ 55-59
3. **ስደት**፡-በሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ውስጥ ያለማቋረጥ ስለ ክርስትያኖች ስደት እናነባለን ። ሐዋ4 ፣ 18 – 21 5፣ 17 – 18 7 ፣ 59 – 60 12፣ 1- 4
4. **መንፈስ ቅዱስ** ፡- የመንፈስ ቅዱስ መውረድና በክርስቲያኖች ውስጥ መኖር ለመጀመርያ ጊዜ የተገለጸው በሐዋርያት ሥራ መጽሃፍ ውስጥ ነው ። ወንጌልን ለመስበክ ድፍረትና ጥበብ ፣ በእስራትና በግርፋት ሁሉ ጽናትን በመንፈስ ቅዱስ ያገኙ ነበር ። ሐዋ 2 ፣ 1-4 ፣ 41

## ጥናት 1: የኢየሱስ ወደ ሰማይ ማረግ

የምንባብ ክፍል ፤ ሐዋ 1 ፣ 1-11

መግቢያ

ከትንሳኤው በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አርባ ቀናት ያህል አብሮ በማሳለፍ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ከነገራቸውና ስለ ትንሳኤው በብዙ ማስረጃ ካረጋገጠላቸው በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁና ኃይልን ተቀብለው የእርሱ ምስክሮች እንደሚሆኑ ነግሯቸው እነርሱ እያዩ ወደሰማይ ማረጉን እንመለከታለን ።

የመወያያ ጥየቄዎች

1. ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ ያሳለፈው ለስንት ቀናት ያህል ነበር?
2. ኢየሱስ ባሳለፈባቸው ቀናቶች ያደረጋቸው ዋና ዋና ነገሮች ምን ምን ነበሩ? (ቁ 3-5)
3. ኢየሱስ በብዙ ማስረጃ ስለትንሳኤው ያሳየቸው ለምን ይመስልሃል/ሻል?
4. በክርስትና እምነት ውስጥ ትንሳኤ ዋንኛ የሆነው ለምን ይመስልሃል/ሻል? 1ኛቆሮ 15 ፣ 7ጋር አመሳክር።
5. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ ያዘዛቸው ለምን ነበር?
6. አብ የሰጠውና ኢየሱስ የተናገርው የተስፋ ቃል ምንድነው?
7. መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ላይ ሲወርድ ምን ያደርጋል?
8. ሁለት ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች (መላእክት) ደቀ መዛሙርቱን ምን አሏቸው?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

9. በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅህ እርግጠኛ ነህ (ሽ) ን?
10. አንተ (ቺ) የሐዋ 1 ፣ 8 ን የምትፈጽመው/ሚው እንዴት ነው?
11. የኢየሱስን ምጻት እየጠበቃችሁ ያላችሁት እንዴት እንደሆነ ተነጋገሩ።
12. የኢየሱስ ትንሳኤ ለአንተ/አንቺ ምን እንደሆነ ተናገሩ ።

ማጠቃለያ

ከሞት የተነሳውና ወደሰማይ ያረገው ኢየሱስ ተመልሶ ስለሚመጣ ምስክሮቹ እንድሆን የተሰጠንን ሃላፊነት እንዳንዘነጋ ክፍሉ ያሳስበናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። “ሐዋ1 ፤ 8

## ጥናት 2: የማትያስ መመረጥ

የምንባብ ክፍል ፤ሐዋ 1፣ 12-26

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ከትንሳኤው በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አርባ ቀናት ያህል አብሮ በማሳለፍ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ከነገራቸውና ስለ ትንሳኤው በብዙ ማስረጃ ካረጋገጠላቸው በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁና ኃይልን ተቀብለው የእርሱ ምስክሮች እንደሚሆኑ ነግሯቸው እነርሱ እያዩ ወደሰማይ ማረጉን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በይሁዳ በታ ከአስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር የትንሳኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ስለ ተተካው ስለ ማቲያስ መመረጥ እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የደብረ ዘይት ተራራ ከኢየሩሳሌም ያለው ርቀት ምን ያህል ነው?
2. ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ወደ ሚኖሩበት ሰገነት ከገቡ በኋላ ምን ያደርጉ ነበር?
3. ደቀ መዛሙርቱን ጨምሮ አብረው በኢየሩሳሌም የነበሩ ቁጥራቸው ስንት ነበር?
4. ይሁዳ ኢየሱስን በሸጠው ገንዘብ ምን አደረገበት? እርሱስ በምን ዓይነት መንገድ ሞተ?
5. ለትንሳኤው ምስክር እንዲሆኑ ዕጣ የተጣለላቸው ወገኖች መስፈርታቸው ምን ምን ነበር?
6. ዕጣ ከመጣሉ በፊትስ በእግዚአብሔር ፊት የጸለዩት ጸሎት ምን ነበር?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጌታ እራሱ አገልጋዮችን እንዲሾም ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት ትላለህ/ትያለሽ? ቤተክርስቲያንስ ማን ናት?
8. በአንድ ልብ ሁኖ በጸሎት መትጋት ለቤተ ክርስቲያን ምን ጥቅም እንዳለው ተነጋገሩ ።
9. ዛሬ እኛ በምንገኝበት ዘመን ሐዋርያ ተብለው የሚሾሙትን እንዴት ይመለከቱታል? ቁ 24-26

ማጠቃለያ

እውነተኛ አገልጋይ የሚሾመው በእግዚአብሔር በራሱ ስለሆነ የሰው እጅ ጣልቃ ሳይገባ የእግዚአብሔር ፈቃድ መጠየቅ አለበት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር ባንድ ልብ ሆነው በጸሎት ይተጉ ነበር።” ሐዋ 1፣14

## ጥናት 3: የመንፈስ ቅዱስ መውረድ

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 2፣ 1-13

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በይሁዳ ቦታ ከአስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር የትንሳኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ስለ ተተካው ስለ ማቲያስ መመረጥ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እንደወረደባቸውና እንደሞላባቸው እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ምን ያደርጉ ነበር?
2. ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት የሞላው ምን ነበር? ምን አይነት ልሳኖችስ ታዩአቸው?
3. መንፈስ ቅዱስ በስንቶቻቸው ሞላባቸው? በሌላ ልሳኖች የተናሩትስ እንዴት ነበር?
4. በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ምን ዓይነትና ምንስ ሲያደርጉ ነበር?
5. የገዛ ቋንቋቸውን በልሳን ሲናገሩ የሰሙ የስንት አገር ሕዝቦች ነበሩ? የሰሙትስ ፍሬ ነገር ምን ነበር?
6. ያፌዙት ሰዎችስ የሰሙትን ነገር ምን ብለው ተረጎሙት?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. ስለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጸልየህ ታውቃለህ?
8. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በክርስቲያኖች ህይወት የሚያመጣው ለውጥ ምን እንደሆነ ተነጋገሩ።
9. ዛሬስ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበልን እርግጠኛ የምሆነው እንዴት ነው?

ማጠቃለያ

በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት በአንድ ልብ ሆኖ መጸለይና መጠየቅ ያስፋልጋል ።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፣መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።” ሐዋ 2፣4

# ጥናት 4: የጴጥሮስ ስብከት

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 2 ፣ 14-41

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በበዓለ ሃምሳ ቀን በሐዋርያትና አብረው በአንድ ልብ በነበሩ ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደባቸው ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጴጥሮስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ስለ ኢየሱስና ስለ መንፈስ ቅዱስ በማስረዳት የንስሃ ጥሪ ስበከት እንደሰበከ እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጴጥሮስ መልእክቱን ያቀረበው ለማን ነበር?
2. የጠቀሳቸው የትኞቹን የነብያት መጽሃፍት ነው? የጠቀሰውስ ምንን ለማስረዳትና ለመግለጽ ነበር?
3. የጴጥሮስን ስብከት በአንድ ሃሳብ የሚያጠቃልለው ቁጥር የቱ ይመስልሃል? እንዴት? ቁ 33
4. ምን ማድረግ አለብን ሲሉ የጴጥሮስ መልስ ምን ነበር? (ቁ 37-39)
5. በጴጥሮስ ስብከት ስንት ነፍስ ተጨመረ? ወደ ሐዋሪያት ህብረት የተጨመሩት ሰዎችስ ምን ምን ያደርጉ ነበር? (ቁ 40 – 41)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. ጴጥሮስ በመንፈስ ተሞልቶ ያደረገው ስብከት በሕይወትህ ምን ትርጉም አለው?
7. ለሌሎች መዳን የምትመሰክርበት ጊዜ አለህን? ምስክርነትህስ ከጴጥሮስ መልእክት ጋር ምን ያህል ይመሳሰላል?

ማጠቃለያ

ነፍሳት በጌታ ድነው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲጨመሩ መንፈስ ቅዱስን በመሞላት ላልዳኑ ሰዎች ወንጌልን መስበክ የሁሉም አማኝ ኃላፊነት ነው።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ንስሃ ግቡ ሃጢያታችሁም ይሰርይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” ሐዋ2፣38

# ጥናት 5: የአማኞች የህብረት ኑሮ

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 2 ፣ 42-47

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጴጥሮስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ስለ ኢየሱስና ስለ መንፈስ ቅዱስ በማስረዳት የንስሃ ጥሪ ስበከት እንደሰበከ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእነዚህ አማኞች የህብረት ኑሮ እንዴትና ምን ይመስል እንደነበር በዝርዝር እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 42 እንደምንመለከተው አማኞቹ ይተጉ የነበረው በምን ምን እንደ ነበር በዝርዝር ተነጋገሩ።
2. በሐዋርያት እጅግ ብዙ ድንቅና ምልክት በመደረጉ በሰው ሁሉ የሆነው ምን ነበር? ይህስ ምን ማለት ነው?
3. ከቁ44-46 ላይ እንደምንመለከተው አማኞች በመሃከላቸው የነበረውን እውነተኛ የልብ አንድነት የገለጹባቸው መንፈሳዊና አካላዊ ህብረቶች ምን ምን አብሮ በማድረግ እንደነበር ተነጋገሩ።
4. ይህንንስ የአንድ ልብ ህብረት በትጋት ይፈጽሙት የነበረው በየምን ያህል የቀንናት ልዩነት ውስጥ ነበር?
5. በቁ 46 ላይ በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ ሲል ምን ማለት ነው? (ፍንጭ: በመቅደስ…በቤታቸውም)
6. በቁ 47 ላይ እንደምንመለከተው ይህ የአማኞቹ እውነተኛ የልብ አንድነትና የየዕለት ትጋት ምን አይነት መልካም ፍሬ እንዳፈራ በመጥቀስ ተነጋገሩ።

ሕይወት ጋር ማዛመድ

7. በዚህ ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን የአማኞች እውነተኛ ኅብረት ምን ያህል ይገለጣል ብለህ ታስባለህ?
8. በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ይሁን በአሕዛብ ዘንድ ጎልቶ የሚወጣው አንድነትዋ ወይስ መከፋፈልዋ? ለምንስ ይመስልሃል?
9. በዚህ ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን እንደ መጀመሪያዋ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አግዚአብሔር አምላክ የሚመሰገንበት፣ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ ዘንድ ሞገስ የምታገኝበትና ብዙ ነፍሳት የሚጨመሩባት እንድትሆን ምን መደረግ አለበት ትላለህ? በዚያ ውስጥ ያንተስ አስተዋፅዖ ምን ይመስልሃል?

ማጠቃለያ

በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የአማኞች የልብ አንድነት ሁለንተናዊ ኅብረት መሆኑን ይኸውም በእግዚአንብሔር ቃል ትምህርት፣በጸሎትና እንጀራንም አብሮ በመቁረስ ይገለጥ የነበረና በየዕለቱም በትጋት ይፈጸም እንደነበረ ከክፍሉ ተመልክተናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በጸሎቱም ይተጉ ነበር ።” ሐዋ 2:42

# ጥናት 6: የሽባው ሰው መፈወስና የጴጥሮስ ስብከት

የምንባብ ክፍል ፤ ሐዋ 3፣1-26

መግቢያ

ባለፈው ጥናት የአማኞች የህብረት ኑሮ እንዴትና ምን ይመስል እንደነበር በዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በቤተ መቅደስ ደጅ ይለምን የነበረውን የአካል ጉዳተኛ ሰው ሐዋርያው የጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደፈሰውና ይህን ፈውስ ላዩት ሰዎች ንግግር እንዳደረገ እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ የሄዱበትን ሁኔታና ያጋጠማቸውን ጉዳይ በዝርዝር አስረዳ?
2. በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጴጥሮስ ያደረገው የፈውስ አገልግሎት እንዴት እንደተፈጸመና የተፈወሰው የአካል ጉዳተኛ ምላሽ እንዴት እንደነበር አስረዳ?
3. በቤተ መቅደስ የነበሩት ሰዎች ይህን ፈውስ ተመልክተው ምን ተሰማቸው? ከማር 16፣17 ጋር በማንበብ ያነፃፅሩ ፡፡
4. እንግዲህ እናንተም እንደአለቆቻችሁ ባለማወቅ ያደረጋችሁት ሃጢያት እንዲደመሰስ ምን ማድረግ አለባችሁ ሲል ጴጥሮስ አስረዳቸው? (17-19)
5. እግዚአብሔር አስቀድሞ በቅዱሳን ነብያት አፍ በሙሴ እንዲሁም ከሳሙኤል ጀምሮ በተነሱት ነብያት ሁሉ ሊመጣ ስላለው መሲህ ከተናገረው መሃል በክፍሉ የተጠቀሰውን ሃሳብ ዘርዝረህ አስረዳ።
6. እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘርህ በምድር ወገን ሁሉ ይባረካሉ ያለው ትንቢት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት እንደተፈጸመ አስረዳ። ሐዋ 3፣25 ከ ዘፍ 12፣ 1-3 ጋር በማነጻጸር ያንብቡ።

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. በስጋ ደዌና በተለያዩ በሽታዎች የሚደረግ የፈውስ አገልግሎት ላይ ጸሎት በተለይም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ያለውን ድርሻ አስረዳ?
8. ይህን በመሰለ አገልግሎት ውስጥ ያየኸውንና/ሽውን ያሳለፍክበትን/ሽበን ተሞክሮ አካፍል/ይ?
9. ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ሲመላለስ እንዳላወቁት ሁሉ ዛሬም ስለ ኢየሱስ በሚገባ ያልተረዱና የማያውቁ ሰዎች እንዳሉ በመረዳት ምን ያህል ለወንጌል ስርጭት ትጥራለህ? ተሞክሮህን አካፍል።

ማጠቃለያ

በመጀመሪያ የነበረችው የአማኞች ህብረት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የተነቃቃችና በሙሉ እምነት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሳኤውን በማወጅ በጌታ ስም ድንቅና ታምራትን እያደረገች ያላመኑ ሰዎችን ከማስደመም አልፋ በጌታ አምነው እንዲድኑ የምታደርግ ጉባኤ ነበረች ። በዛሬይቱም ቤተ ክርስቲያን ይህ የጌታ የማዳን ሥራ እንዲቀጥልና አብዝቶ እንዲታይ ለእኛ ለሁላችን በተሰጠ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል አማካይነት ላልዳኑ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት በመመስከር በወንጌል ስርጭት ዘወትር ልንተጋ ይገባል ።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:

"እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነብያት አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው።" ሐዋ 3፡18

## ጥናት 7: ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 4፡1 - 22

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በቤተ መቅደስ ደጅ ይለምን የነበረውን የአካል ጉዳተኛ ሰው ሐዋርያው ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደፈሰውና ይህን ፈውስ ላዩት ሰዎች ንግግር እንዳደረገ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዴት ተይዘው በአይሁድ ሸንጎ ፊት እንደቀረቡና ያጋጠማቸውንም ሁኔታዎች በዝርዝር እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሐዋርያት በኢየሱስ ስለተገኘው ትንሳኤ ሙታን ለህዝቡ መስበካቸው ካህናትንና የቤተ መቅደስ ሀላፊዎችን ፣ እንዲሁም ሰዱቃውያን ያስቆጣቸው ለምን ነበር? ምንስ እርምጃ ወሰዱ? (ቁ1-4)
2. በቀጣዩ ቀን (በማግስቱ) በቤተ መቅደስ ካህናትና ሃላፊዎች እንዲሁም ሰዱቃውያን ፊት ጴጥሮስና ዮሐንስ የተጠየቁት ጥያቄና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ኢየሱስን በማክበር የሰጡት ምላሽ ምን ነበር? (ቁ 5-10)
3. ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን እራስ ሆነ የሚለው ትንቢታዊ አባባል ኢየሱስን እንዴት አድርጎ እንደገለጸው አስረዳ?
4. በቁ 12 ላይ ድነት በሌላ በማንም አይገኝም ሲል ምን ማለቱ ነው? ከሐዋ 10፣43 እና 1 ጢሞ 2፣5-6 ጋር በማንበብ ያነጻጽሩ።
5. የአይሁድ ሸንጎ የመጨረሻው ውሳኔ ምን ነበር? ይህን ውሳኔ ለመወሰን ያነሳሳቸው ምክንያት ምንድን ነው? የጴጥሮስና ዮሐንስ ምላሽስ ምን ነበር?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. ሐዋርያትን በድፍረት ሊመሰክሩለት የወደዱት ጌታ የእኛም ጌታ መሆኑን እንደ ሐዋርያቱ ምን ያህል በሰዎች ፊት በጥበብና በድፍረት የትንሳኤውን እንመሰክራለን?
7. ከመሰከርንስ ያገኘነውን ምርኮ ለእግዚአብሔር ክብር ለቡድን አካፍል።

ማጠቃለያ

ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ ወህኒ ያስጣላቸው ጉዳይ ዲያቢሎስ ሊነገር የማይወደውን እውነት ይኸውም የኢየሱስን ክርስቶስነት በይፋ ማወጃቸውና እንዲሁም ሞቱንና ትንሳኤውን ለሌሎች መመስከራቸው ነበር። ዲያቢሎስ በዚህም ዘመን ቢሆን ከቀድሞው በከፋ መልኩ በማንኛውም መንገድ ተግዳሮት ማበጀቱ መቼም ቢሆን የማይቀር ነው።እኛም ከዚህ በመማር የመንፈስ ቅዱስን አቅምና ጉልበት በመታመን በጥበብና በድፍረት የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ በዚህም የተገለጠውን የህይወት ብርሃን ለሌሎች በማወጅ የተሰጠንን የወንጌል አደራ በታማኝነት ልንወጣ ይገባል ።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“መዳንም በሌላ በማንም የለም ፤እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ ሌላ የለምና።” ሐዋ 4፡12

## ጥናት 8: የአማኞች ጸሎትና ማኅበራዊ አኗኗር

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 4፡ 23-37

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዴት ተይዘው በአይሁድ ሸንጎ ፊት እንደቀረቡና በጌታ ስም በመናገራቸው የደረሰባቸውን እስራትና ዛቻ ያጋጠማቸውንም ሁኔታዎች በዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጴጥሮስንና ዮሐንስ ከአይሁድ ሸንጎ ከታሰሩበት ከተፈቱ በኋላ ከወገኖች ጋር ያደረጉትን ጸሎት እንዲሁም በጊዜው አማኞች ስለ ነበራቸው ማህበራዊ አኗኗር እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎና በወህኒ ስላደረጉት ቆይታ ለወገኖች ካስረዱ በኋላ ወደ ጸሎት መሄዳቸው ስለ ተለማማዱት ህይወት ምን ያመለክትሃል?
2. የጴጥሮስንና የዮሐንስን መፈታት አስመልክቶ የተሰበሰቡ ወገኖች የጸለዩትን በትንቢት የተደገፈ ጸሎትና ከጸለዩትም ጸሎት የተነሳ የተከናወነውን ተአምራትና የመንፈስ ቅዱስ ስራ አስረዳ?
3. ስለ ኢየሱስ መምጣትና መከራን መቀበል አስቀድሞ ማን እንደወሰነ ይናገራል? ቁ 27-28
4. ያመኑት ሁሉ በአንድ ልብና በአንድ ሃሳብ ተስማምተው ነበር ሲል ምን ዓይነት ህብረትን ያመለክታል? (ቁ 32)
5. በበጎ ፈቃድ ያላቸውን ቤትና መሬት በመሸጥ ወደ ሐዋርያት አምጥተው መስጠታቸው በጊዜው ለነበረችው የአማኞች ህበረት ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነቱ ምን ያህል ይሆናል ብለህ ትገልጻለህ (ቁ 34-35)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. የዲያብሎስን ስራ ሊያፈርስ የሚችለውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማወቅ ምን ያህል እንጠቀምበታለን? ያለፈቃዱስ ምንም እንደማይሆንብህ ታውቃለህ?
7. ዛሬ ባለንበት ዘመን ላለችው ክርስቲያን መንፈሳዊ አንድነት ከጸሎትና የጌታን ስም ከመጥራት ባሻገር ማድረግ ያለብን ተግባራዊ ነገር ካለ ለቡድንህ/ሽ/ አካፍል/ይ ።
8. በዘመናችን ባለንበት አገርና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ስለ ጌታ ሲሉ ዋጋ ለሚከፍሉ እንዲሁም በተለያዩ ችግሮች ስለሚያልፉ ወገኖች ግድ ብሎን በጸሎትና በሌላውም አስፈላጊ ድጋፍ ምን ያህል አብረናቸው እንቆማለን?

ማጠቃለያ

አምላካችን የሁሉ የበላይ ባለ ስልጣን ሁሉም ሊሰሙት የተገባ ጌታ በመሆኑ ሁኔታዎችን ሁሉ በእርሱ ፈቃድና በጌትነቱ ስር ለማስቀመጥ ፍቃዱን ለማገልገል ህብረት እንድናደርግ ያስተማረውን ቃሉን አምነን ከወገኖች ጋር በእውነተኛ አምልኮና በጸሎት አብረን ልንተጋ ተጠርተናል ። በመሆኑም በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት በታማኝና ቃል አክባሪ በመሆን የበርናባስን አይነት የመጽናናት ምሳሌ ህይወት ልንኖር ይገባናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:

«ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ኃይል ነበረባቸው።" ሐዋ 4፣33

## ጥናት 9: ሐናንያና ሰጲራ

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 5 ፡ 1- 11

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ጴጥሮስንና ዮሐንስ ከአይሁድ ሸንጎ ከታሰሩበት ከተፈቱ በኋላ ከወገኖች ጋር ያደረጉትን ጸሎት እንዲሁም በጊዜው አማኞች ስለ ነበራቸው ማህበራዊ አኗኗር ተመልክተን ነበር ።በዛሬው ጥናታችን ደግሞ አማኞች መንፈስ ቅዱስ በመካካላቸው በሙላት እየሰራ በነበረበት ወቅት አንዳንድ ወገኖች ስለገጠማቸው የሰይጣን ስጋዊ ፈተናና እና የመንፈስ ቅዱስን ፍርድ እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሐናንያና ሰጲራ የተባሉት ባልና ሚስት መሬታቸውን ለመሸጥ ያነሳሳቸው ነገር ነበር? ካለፈው ጥናት (ሐዋ 4 ፣ 36-37) በርናባስ ካደረገው ጋር ልዩነቱ ምንድር ነው?
2. ሐናንያና ሰጲራ ከሽያጩ ያስቀሩበት ምክንያቱ ምንድር ነው ብለህ ታስባለህ?
3. ሰይጣን በልቡ ከመሙላቱ የተነሳ በሐናንያ አድራጎት የተታለለው ጴጥሮስ ቢሆንም መንፈስ ቅዱስን አታለልክ መባሉን ስትመለከት ስለመንፈስ ቅዱስ ስብእና ምን ያስረዳል? ስለ ሰይጣንስ አሰራር ምን ያስተምርሃል?
4. መሬቱ ቀድሞውንም ቢሆን የራሳቸው በመሆኑ ባልና ሚስት የመሬታቸውን ሽያጭ ገንዘብ የተወሰነ መጠን ቀንሰው መስጠት ወይም ፈጽሞ አለመስጠት ይችሉ የነበረ ይመስልሃል? ወይስ አይችሉም ነበር? ለምን?
5. የከፋ ኃጢአት የሆነባቸውስ ከሽያጩ እኩሌታውን ማስቀረታቸው ነው ወይስ በሰው ፊት ሙሉውን እንዳቀረቡ በማስመሰል በውስጥ ማንነታቸው ግን መንፈስ ቅዱስን መዋሸታቸው ነው ተነጋገሩበት።?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. የህይወት ቅድስና እና የመንፈስ ቅዱስ ህልውና በኃይል ባለበት ስፍራ ሀጢያት መቆም አለመቻሉን ምን ያህል አስተዋልክ?
7. ዛሬ እንደዚህ አይነት ነገር ቢፈጠር ቤተ ክርስቲያን ምን የምትሆን ይመስልሃል? በውጪ ያሉትስ ሁኔታውን ቢሰሙ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ምን የሚሉ ይመስልሃል?
8. እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ሆኖ በህዝቡ ይፈርዳል ይላል ይህንን ከክፍሉ ጋር በማያያዝ ተወያዩበት። (በዕብ 10፣31 እና 1ቆሮ 5፣5)

ማጠቃለያ

የምናመልከው አምላካችን ጻድቃን ሳንሆን መስለን ያልሆነውን ሆነን እንድንታይ ሳይሆን በፍቅር ላይ ተደግፈን በንፁህና እርሱ በሚያውቀው እውነተኛ ማንነታችን ያለ ግብዝት ወደ እርሱ በመቅረብ እንድናመልከው ይፈልጋል ።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል። “ዮሐ 4፣24

## ጥናት 10: የሐዋርያት አገልግሎትና መከራን መቀበል

የምንባብ ክፍል ፤ ሐዋ 5፣ 12-42

መግቢያ

ባለፈው ጥናት አማኞች መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው በሙላት እየሰራ በነበረበት ወቅት ሐናንያና ሰጲራ የተባሉት ባልና ሚስት ስለገጠማቸው የሰይጣን ስጋዊ ፈተናና እና የመንፈስ ቅዱስን ፍርድ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔር የምህረት ስራውን በሐዋርያት ሲሰራና የደረሰባቸውን ተቃውሞና የእነርሱን ጽናት እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሐዋርያቶች የነበራቸው የልብ አንድነት ምን ይመስል ነበር? በአገልግሎቶታቸው የታዩትን ምልክቶች ዘርዝር።
2. ከአገልግሎታቸው የተነሳ በቁጥራቸው ላይ ምን አይነት ለውጥ መጣ? ሌሎች ሊተባበሯቸው ያልደፈሩት በምን ምክንያት ነው?
3. ሊቀ ካህናት ሐዋርያቶቹን ያሰሩበት ምክንያቱ ምንድነው? እነርሱስ ተመልሰው ወንጌልን መናገር እንዴት ቻሉ?
4. በሸንጎ ፊት በቀረቡ ጊዜ የክሳቸው ዋና ሐሳብ ምን ነበር? የሐዋርያትስ ምላሽ ምን ነበር?
5. ተገርፈውና ተዝቶባቸው ከተለቀቁ በኋላ የተሰማቸው ስሜት ምን ይመስል ነበር? ከዚያ በኋላ ኑሮአቸው ምንን ያሳይ ነበር?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. አንተ/አንቺ እነደ አንድ አማኝና በጋራ ደግሞ እንደ ቤተ ክርስትያን የህልውናችን ዋና ተልእኮ የምሰራቹን መናገር መሁኑን ምን ያህል ተረድተሃል/ሻል?
7. በቁ39 ላይ እንደምንመለከተው ተመለከትነው ገማልያል የተባለው የከበረ የሕግ መምህር የነበረው ሰው «ከእግዚአብሔር የሆነን ስራ ማንም ሊያጠፋው እንደማይችል» መናገሩ በኑሮና በአገልግሎት እንቅፋቶች ቢኖሩም ማንም እንደማይቋቋምህ አንተስ /ቺስ ምን ያህል ተረድተሃል/ሻል?

ማጠቃለያ

የወንጌልን ቃል መናገር የህይወታችን ዋና ተልእኮ መሆኑን በመረዳት ባገኘነው አጋጣሚ ክርስቶስን ባለ ማወቅና ባለመቀበል ለሚጠፋው ዓለም የመናገር ጥሪ ብቻ ሳይሆን የጌታ ትእዛዝ እንደሆነ በመረዳት ሁል ጊዜ በትጋትና በታማኝነት ተልዕኮአችንን ልንወጣ ይገባል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"ዕለት እለትና በመቅደስ በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተውም ነበር።" ሐዋ 5፣42

# ጥናት 11: የሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ

የምንባብ ክፍል፤ የሐዋ 6: 1-7

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ሐዋርያት የደረሰባቸውን ውጫዊ ተቃውሞና ጫና ሁሉ ተቋቁመው በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና መሪነት ያደረጉትን በድንቅና በተአምራት የተታጀበ ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በኢየሩሳሌም አማኞች መካከል ስለ ተፈጠረው ቅሬታና ለመፍትሄውም ስለ ተወሰደው እርምጃ ይኸውም ስለ ሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢየሩሳሌም ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው በነበሩት አይሁድና በይሁዳ ይኖሩ በነበሩት አይሁድ መሃከል የተፈጠረው ችግር ምንድር ነው? የችግሩ መንስዔስ ምን ነበር? (ቁ 1)
2. አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለተፈጠረው ችግር ያቀረቡት የመፍትሄ ሐሳብ ምን ነበር? ራሳቸውን ደግሞ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን ሲሉ ምን ማለታቸው ይመስልሃል? ሐዋ6:4ን ከማቴ 28:19-20 ና ከማር 16:15-20 ጋር በማነፃፀር ያንብቡት።
3. የሚመረጡት ሰባት ሰዎች ከራሳቸው መካከል መሆናቸውና መስፈርቱ ደግሞ በመልካም የተመሰከረላቸው፥ መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸው እንዲሆኑ መፈለጉ ምን ማለት እንደሆነ በዝርዝር ተወያዩበት። (ቁ3).
4. አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ያቀረቡትን የመፍትሄ ሐሳብ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት እንዴት ተመለከቱት? ምን ዓይነትስ ተግባራዊ ምላሽ ሰጡ? (ቁ5.)
5. የተመረጡት ሰዎችስ እነ ማን ነበሩ? ምንስ ተደረገላቸው? ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን መጫናቸው ምን ዓይነት መንፈሳዊ ትርጉም ያለው ይመስልሃል? (ከቁ5-6)
6. አሥራ ሁለቱ ሐዋርትያትና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ይህን በማድረጋቸው ለወንጌል መስፋፋትና በኢየሩሳሌምም የደቀመዛሙርት ቁጥር ላይ ምን ዓይነት አስትዋጽኦ ነበረው?
7. ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ ይላል። በዘመኑ ካህናት በወንጌል ላይ ምን ዓይነት አቋም የነበራቸው ሰዎች ነበሩ? የእነዚህ ሰዎች መለወጥ የወንጌልን አሸናፊነት እንዴት እንድትረዳው ያደርግሃል?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

8. ዛሬም በዘመናችን የተለያዩ ውስጣዊ አለመግባባቶች በቤተ ክርስርስቲያን በሚፈጠሩበት ወቅት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣት ዋነኛ የወንጌል አደራ እንዳይተጓጎል ምን መደረግ አለበት ትላለህ? በዚህ ውስጥ ያንተስ ድርሻ ምንድር ነው?
9. የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን መስራቾች የሆኑት የጌታ ተከታዮች የደረሰባቸውን ልዩ ልዩ ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች ተቋቁመው ለጸሎትና ለቃሉ አገልግሎት ትልቅ ስፍራ ከመስጠታቸው የተነሳ ወንጌል እጅግ ሲስፋፋና ብዙ ነፍሳትም ሲድኑ መመልከታችን እኛስ በዚህ መጨረሻ ዘመን ምን እንድናደርግ ያስተምረናል?

ማጠቃለያ

በአማኞች መካካል ለተፈጠረው ችግር አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ያቀረቡትን የመፍትሄ ሐሳብ ከሌሎቹ አማኞች/ደቀ መዛሙርት / ጋር ተቀባብለው መፍታት ከመቻላቸው የተነሳ ወንጌል ምን ያህል እየሰፋ እንደሄደና ተቃዋሚ የነበሩ ካሕናት እንኳ ሳይቀሩ መለወጣቸውን ተመልክተናል ። በመሆኑም ዛሬም በዘመናችን በክርስቲያኖች መካከል ለሚከሰቱ ልዩ ልዩ ችግሮች አገልጋዮችና አማኞች ምዕመናን ሁሉ እነደ እግዚአብሔር ቃል በአንድ ሐሳብ ተስማምተው መፍትሄ ቢያቀርቡና መንፈሳዊ እርምጃ ቢወስዱ ለወንጌል መስፋፋትና ለነፍሳት መዳን ትልቅ አስተዋጽዖ ያበረክታል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።" ሐዋ 6:4

## ጥናት 12: የእስጢፋኖስ መያዝ

የምንባብ ክፍል፤ የሐዋ 6: 8-15

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በኢየሩሳሌም አማኞች መካከል ስለ ተፈጠረው ቅሬታና ለመፍትሄውም ስለ ተወሰደው እርምጃ ይኸውም ስለ ሰባቱ ዲያቆናት መመረጥና ከዚያም በኋላ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያደረጉትን ወንጌልን የማስፋፋት አገልግሎት ተመልክተን ነበር።በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ከተመረጡት ከሰባቱ ውስጥ አንዱ የነበረው እስጢፋኖስ ስላካሄደው የወንጌል አገልግሎትና ይህንንም ተከትሎ በተቃዋሚዎች ስለ ተደረገበት ሤራና በመጨረሻም ስለመያዙ እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. እስጢፋኖስ በሕዝብ መከከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን እንዲያደርግ ያስቻለው ነገር ምን ስለሆነ ነበር? (ሐዋ (ቁ8ን ከሉቃ4:1 ጋር በማነፃፀር ያንብቡት)
2. እስጢፋኖስን ይከራከሩት የነበሩት ሰዎች እነማን ነበሩ? ሊቋቋሙት ያልቻሉትስ ምኑን ነበር? (ቁ 9-10ን ከሉቃ 12:11-12 ጋር ያነጻጽሩ)
3. እነዚሁ ሰዎች በእስጢፋኖስ ላይ በማሤር ሐሰተኛ ምስክሮችን በስውር ማሰናዳታውቸው በክፍሉ ተጠቅሷል። እነዚህ የቀረቡት የሐሰት ውንጀላዎች ምን ምን የሚሉ ነበሩ? (ከቁ11-14)
4. እስጢፋኖስ በወንጌል ተቃዋሚዎች የሐሰት ክስ አማካኝነት ተይዞ ሸንጎ ፊት ቀርቧል። ይህ ሸንጎ ያካተታቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እነ ማን ነበሩ? (ቁ12) ። እንዲህ ዓይነት ሰዎች መካተታቸው ለምን ይመስልሃል?
5. በሸንጎው የተቀመጡት ሁሉ ትኩር ብለው ሲመለከቱት የእስጢፋኖስን ፊት እንደ መልዓክ ፊት ሆኖ አዩት። ይህስ የሆነው ለምን ይመስልሃል? (ቁ15)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. በዚህ ዘመን ለወንጌል አገልግሎት በግልም ሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል እየተንቀሳቀስን እንገኛለን?
7. በዚህ ዘመን ባለንበትም አገር ይሁን በሌሎች የዓለም ክፍሎች በወንጌል ምክንያት በሐሰት የተከሰሱ ዐብያተ ክርስቲያናት ወይም ተይዘው በእስር ላይ የሚገኙ ክርስቲያኖች እንዳሉ ታውቃለህ?
8. ተቃዋሚዎች ቤተ ክርስቲያንን መቋቋም እንዳይችሉና ወንጌልም እንዲስፋፋ የመንፈስ ቅዱስን ኀይል መታጠቅ አስፈላጊነቱን ከከፍሉ ምን ያህል ተረዳህ? ከዚህ በመነሳት አንተስ ካሁን በኋላ ምን ልታደርግ ወሰንክ?

ማጠቃለያ

የወንጌል አገልግሎት ሊያስከትል የሚችለውን ተቃውሞና በአንፃሩም ደግሞ አማኞች የመንፈስ ቅዱስን ኀይል መታጠቅ ለወንጌል መስፋፋት ያለው ድርሻ ይህን ያህል ታላቅ መሆኑን ከእስጢፋኖስ ሕይወትና አገልግሎት ተመልክተናል።በመሆኑም በየትኛውም ዘርፍ ውስጥ ጌታንና ህዝቡን የምናገለግል ሁሉ አገልግሎታችን ምን ጊዜም ቢሆን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ልናከናውነው ይገባዋል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ምልክትን ያደርግ ነበር።" ሐዋ6:8

## ጥናት 13: እስጢፋኖስ በሸንጎ ፊት ያደረገው ንግግር እና መወገር

የምንባብ ክፍል ፤የሐዋ 7: 1-59

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ከተመረጡት ከሰባቱ አንዱ የነበረው እስጢፋኖስ ስላካሄደው የወንጌል አገልግሎትና ይህንንም ተከትሎ በተቃዋሚዎች ስለ ተደረገበት ሤራና ስለመያዙ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እስጢፋኖስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት የተናገረው የመከላከያ ቃል በክርስቶስና በሐዋርያት የተሰበከውን ወንጌል የሚደግፍና ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚቃወሙትን በመከላከሉ ምክንያት የከበረ ዓላማ ክቡር ሕይወቱን በሰማዕትነት አሳልፎ መስጠቱን እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ 1-50 ባለው ክፍል እስጢፋኖስ በንግግሩ ላይ ከጠቀሳቸው በርካታ ክፍሎች የተወሰኑትን ከየትኞቹ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት እንደሆኑ ለመዳሰስ ሞክሩ።
2. እስጢፋኖስ ለአይሁድ ሸንጎ ያቀረበው የመከላከያ ቃል ከተከሰሰበት የሃሰት ክስ አንፃር ሲተያይ ለጉባዔው ምን ዓይነት ተቃራኒ እውነታን አስረግጦ የሚያስጨብጥ ይመስልሃል?
3. በቁ 42 ላይ እግዚአብሔርን በመክዳት ፊታቸውን ራሳቸው ወደ ሰሯቸው ጣዖታት ዘወር በማድረግ የጸኑት የእስራኤል ህዝቦች ተላልፈው የተሰጡት ወደ ምንድር ነው?
4. በቁ 51 ለጉባዔው እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮቻችሁም ያልተገረዘ ያላቸው እነማንን ነው?
5. አባቶቻቸው እንደ ተቃወሙት ሁሉ እነርሱም ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን በመቃወም አባቶቻቸው ካደረጉት ይልቅ በከፋ መልኩ ያደረጉት ነገር ምን ነበር? (ከቁ 52-54 ይመልከቱ) ።
6. መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደ ተቀመጠ ይናገራል (ሐዋ2:34 ማር14:62 ሉቃ22:69 ቆላ 3:4) ። በዚህ ስፍራ ግን በቁ 54 ላይ እንደ ምንመለከተው እስጢፋኖስ የሕይወት አጣብቂኝ ሰዓት ላይ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ ይላል። ኢየሱስ የቆመው ለምን ይመስልሃል? (ከማር 8:38 ከሉቃ 12:8 ከሮሜ 8:34 ከ1ዮሐ2:1 ጋር ያነፃፅሩ) ።
7. በቁ 59 እስጢፋኖስ እየተወገረ በነበረበት ሰዓት ላይ ጌታን በመጣራት ስለ ራሱ ምን ብሎ ጸለየ?
8. በቁ 60 እስጢፋኖስን ተንበርክኮ ስለ ወጋሪዎቹ የጸለየው ጌታ ምን እንዲያደርጋቸው ነበር? ይህ ስለ እስጢፋኖስ የክርስቶስ እውነተኛ ደቀ መዝሙርነት ምን ዓይነትተግባራዊ ትርጉም አለው? (ከሉቃ 23:34 ጋር ያነፃፅሩ) ።

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

9. በዚህ ዘመን ባለንበትም አገር ይሁን በሌሎች የዓለም ክፍሎች በወንጌል ምክንያት በሐሰት የተከሰሱ ወይም ተይዘው በእስር ላይ የሚገኙና ህይወታቸውንም በሰማዕትነት እየሰጡ ያሉ ክርስቲያኖች እንዳሉ ታውቃለህ?
10. ስለ ወንጌል አገልግሎትና ስለ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሕይወት ከከፍሉ ምን ያህል ተረዳህ?
11. አንተስ ስለ ወንጌል ምን ተግባራዊ ነገር ልታደርግ እንደወሰንክ ለቡድንህ አካፍል።

ማጠቃለያ

የወንጌል አገልግሎት የሚያስከትለው ተቃውሞ እስከ ዬት ሊደረስ እንደሚችልና በአንፃሩ ደግሞ እስጢፋኖስ ለጌታ የነበረው ታማኝነትና አደራውንም ለመጠበቅ ሕይወቱን ይሰጥ ዘንድ መፍቀዱ በዚህም ዘመን የምንገኝ ቅዱሳን ልንፈፅመው የሚገባ የእምነት ተጋድሎና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ተግባራዊ ኃላፊነት መሆኑን በአንክሮ ያስገነዝባል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ቃሉ የታመነ ነው እንዲህ የሚለው። ከእርሱ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን። ”2ጢሞ2:11

## ጥናት 14: የፊልጶስ አገልግሎትና ጠንቋዩ ሲሞን

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 8፣1-25

መግቢያ

ባለፈው ጥናት እስጢፋኖስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት የተናገረው የመከላከያ ቃል በክርስቶስና በሐዋርያት የተሰበከውን ወንጌል የሚደግፍና ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚቃወሙትን በመከላከሉ ምክንያት በመ ጨረሻ ለዚህ የከበረ ዓላማ ክቡር ሕይወቱን በሰማዕትነት አሳልፎ መስጠቱን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በኢየሩሳሌም በተነሳው ከባድ ስደት በየቦታው የተበተኑት አማኞች በየሄዱበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን እንደ ሰበኩና በተለይም ፊሊጶስ በሰማርያ ከተማ በድንቅና በተአምራት እንዳገለገለና በኋላም ጴጥሮስና ዮሐንስ አብረውት እንዳገለገሉ እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ በኢየሩሳሌም በነበርችዋ ቤተ ክርስትያን ላይ የተነሳው ከባድ ስደትና መከራን አስመልክቶ ምን እንደተፈጸመና አማኞች /ደቀ መዛሙርት/ ምን እንዳደረጉ አብራራ/ሪ/? (ከቁ 1-4)
2. ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ ሄዶ ምን እንዳደረገና የህዝቡስ ምላሽ ምን ይመስል እንደነበረ ግለጽ። (ከቁ 4-8)
3. ሲሞን የተባለው ሰው ማነው? ህዝቡንስ የሚያስተው እንዴትና ለምን ነበር? (ከቁ 9-13)
4. በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት በፊልጶስ አገልግሎት የሰማርያ ከተማ ሰዎች እንደምን ተለወጡ በሰሙ ጊዜ ምን እርምጃ ወሰዱ? የተከናወነውን ታላቅ አገልግሎት አብራራ/ሪ። (ከቁ 14-17)
5. ሲሞን ሐዋርያት እጃቸውን ጭነው ሲጸልዩ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ን መቀበላቸውን አይቶ በገንዘብ ሊገዛ መሞከሩ ከምን የመነጨ ይመስልሃል? (ከቁ 18-24)
6. ሲሞን ሊያደርገው ፈልጎ ለነበረው ክፉ ሐሳብ የነ ጴጥሮስ ምላሽ ምን ነበር?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ በተነሳው ከባድ ስደትና መከራ የወንጌል ቃል በተበተነበት ቦታ ሁሉ መዳረሱን ስታይ አንተስ በህይወት ሩጫ ውስጥ በምትሄድባቸው ቦታዎችና በምታገኛቸው ሰዎች መሃል ወንጌሉን ትናገራለህ? (ከልምምድህ ለቡድንህ ይጠቅማል የምትለውን አካፍል)
8. ሲሞን ሊያደርገው እንደፈለገው ሰዎች የፈውስንም ሆነ የሌሎች አገልግሎቶችን ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ለራሳቸው ስምና ዝና ሲጠቀሙበት ሲታይ ጴጥሮስ ካደረገው አንጻር ምን አይነት እርምጃ ተገቢ ነው ትላለህ?

ማጠቃለያ

ለጌታ ጨክነው በተነሱ አገልጋዮች ላይ በየዘመናቱ ምንም እንኳን መከራና ችግር ቢያይልባቸውም በመንፈስ ቅዱስ ጣልቃ ገብነትና እርዳታ እነርሱ ለነበሩበት ትውልድ በታማኝነትና የሕይወትን መስዋዕትነት በመክፈል ወንጌልን ከማድረሳቸው የተነሳ ያ እነርሱ የዘሩት የወንጌል ዘር እኛም ጋ ደርሶ ይኸው አድኖናል። በመሆኑም እኛም በተሰጠን ዘመን በማቴ 28፣20 ላይ «እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ» ካለው ጌታ ጋር ሆነን እነ ፊልጶስ በወጡበት ሩጫ ለትውልዳችን የምናደርሰውን የወንጌል ተልዕኮ ከጌታ እንደተረክብን አውቀን የተጣለብንን አደራ በታማኝነት ልንወጣ ይገባል ።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።" ሐዋ 8፣4

## ጥናት 15: ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ

የምንባብ ክፍል የሐዋ 8፤ 26-40

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በኢየሩሳሌም በተነሳው ከባድ ስደት በየቦታው የተበተኑት አማኞች በየሄዱበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን እንደ ሰበኩና በተለይም ፊሊጶስ በሰማርያ ከተማ በድንቅና በተአምራት እንዳገለገለና በኋላም ጴጥሮስና ዮሐንስ አብረውት እንዳገለገሉ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ወደ አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ሲላክና ለዚህ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና መጠመቅ ምክንያት እንደሆነ እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የጌታ መልዐክ ፊልጶስን ባዘዘው መሰረት ምን እንደደረገና ማንን እንዳገኘ ግለጽ?
2. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምነ አይነት ሰው እንደነበርና ወዴት እንደሚሄድ አስረዳ?
3. ጃንደረባ የሚለው ቃል ከምንባቡ ምን ትርጉም አለው?
4. ኢትዮጵያዊው ባለሟል ያነበው የነበረው የነቢዩ ኢሳያስ መጽሃፍ ምንና ስለማን እንደሚናገር አስረዳ።
5. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ «እነሆ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምን ነገር አለ» ብሎ እንዲጠይቅ ያደረገው መረዳት ምንድነው ትላለህ? (ከፊልጶስ መልስ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት) ።

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. ፊልጶስን የጌታ መንፈስ ከወሰደው በኋላ ባለፈባቸው ከተሞች ሁሉ ያደርግ የነበረውን ስትመለከት/ቺ አንተስ/ ቺስ ከዚህ ተግባር ምን ትማራለህ/ሽ?
7. ነፍሳትን ለማዳን ወደ ህይወትህ የሚመጣውን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት አድምጠህ መታዘዝ እንዳለብህና ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያገኘኸውን ግንዛቤ ለቡድንህ/ሽ አካፍል/ይ።
8. የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት እንደሚገባ መረዳታችን በተለይ ለወንጌል ስርጭት ሊጠቅም በሚችልና የሌሎች ሰዎችን የነፍስ ጥያቄ በሚመልስ መልኩ ያለንን ዝግጅት ለቡድንህ/ሽ አካፍል/ይ።

ማጠቃለያ

እግዚአብሄርን የምትፈልግ ነፍስን ጩኸት የሚሰማ ጌታ ፊልጶስን ወደ በረሃ መንገድ እንደላከው ሁሉ ዛሬም የብዙ ነፍሳትን የድረሱልኝ ጩኸት መልስ እንድንሰጥ መንፈስ ቅዱስ ይልከናል። በመሆኑም ለሰዎች የምስራቹን ወንጌል ለማስማት የሚረዳንን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለማድመጥ ልባችንን ልንሰጥ ይገባል ። ቃሉንም ስናጠና ወደ ራሳችን ብቻ ሳይሆን እንደ ራሳችን ለሌሎችም የነፍስ ጥያቄ ጭምር መልስ እንደሚሆን በማሰብ ማጥናታችን የፊልጶስን አይነት አገልግሎት እንድናገለግል ያዘጋጀናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ ።” ሐዋ 8፤37

## ጥናት 16: የሳውል ማመን

የምንባብ ክፍል ሐዋ 9፣ 1-19

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ወደ አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ሲላክና ለዚህ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና መጠመቅ ምክንያት እንደሆነ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእስጢፋኖስ ተወግሮ መሞት የተባበረና ቤተ ክርስቲያንን እያሳደደ ብዙ ክርስቲያን ወገኖችን ወደ ወኅኒ ያስገባ የነበረውን ኃይለኛ አሳዳጅ የነበረውን ሳውል የተባለውን ሰው ጌታ እንዴት እንደተገናኘውና ሕይወቱንም እንደለወጠው እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 1 እና 2 ሳውል በጌታ ደቀ መዛሙርት ላይ ይፈጽማቸው የነበሩት አስከፊ ተግባራት ምን ምን ነበሩ?
2. ሳውል ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ራሱን የገለጠለት እንዴትና ምንስ የሚል ድምጽ በማሰማት ነበር? ለሰማው ድምፅስ ሳውል ያቀረበው ጥያቄ ምን የሚል ነበር?
3. ሳውል ያሳድድ የነበረው የጌታን ደቀ መዛሙርት የነበረ ቢሆንም ጌታ ግን ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል/ሻል?
4. ሳውል ጌታ ሆይ ማነህ ብሎ ለጌታ ካቀረበው ጥያቄና ከሰጠውም ምላሽ እንደምንረዳው ሳውል እያሳደደ የነበረው ጌታን እነደሆነ ሳይረዳ የነበረ ቢሆንም ጌታ ለሰጠው ማስጠንቀቂያ ግን በቁ 6 ላይ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?
5. ከሳውል ጋር በዙሪያው የነበሩት ሰዎች የሳውልን ድምጽ ብቻ እየሰሙ ነገር ግን የጌታን ድምጽና እየሆነ የነበረውን ተአምራት ሳያዩ ሳውል ወድቆ ሲነሳ መታወሩን መመልከታቸው ይኼ ሁሉ በእነርሱ ላይ ምን የሚፈጥር ይመስልሃል/ሻል?
6. ጌታ ሳውልን ምን ማድረግ እንደሚገባው ከነገረው በኋላ ለሃናንያ ደግሞ ስለ ሳውል ሲነግረው ሃናንያ ስለ ሳውል ለጌታ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? ጌታስ ስለ ሳውል አገልግሎት በቁ 15 ለሃናንያ የነገረው ምን ነበር?

ሕይወት ጋር ማዛመድ

7. በአንድ ወቅት ቤተ ክርስቲያንን ያሳድዱ የነበሩ ሰዎች በኋላ ግን በድንቅ ተለውጠው በቀረላቸው ዘመን ለጌታ ታማኝ አገልጋይ የሆኑ ሰዎችን ታውቃለህ/ሽ? የጌታን ሕይወት ለዋጭነት ከራህስ/ሽ የግል ሕይወይት ምስክርነት የምታካፍለው/ዪው ነገር ካለህ/ሽ በአጭሩ ለቡድንህ/ሽ አካፍል/ዪ።
8. ዛሬስ ለሚያሳድዱንና ለማይወዱን ሰዎች ጌታ እንዲገናኛቸው ምን ያህል እንጸልያለን? አምነውስ ሲመጡ እንደ ሃናንያ ሳንጠራጠር አምነናቸው ምን ያህል በፍቅር እንቀበላቸዋልን?

ማጠቃለያ

የፍቅር ጌታ ለሕዝቡ ጋሻ በመሆን ሁል ጊዜ ጣልቃ እየገባ ከጠላት ጥቃት ልጆቹን ይታደጋል።ሳያውቁም በከንቱ ቅንዓት ተነሳስተው የቤተ ክርስቲያን አሳዳጆች የሆኑትን በደማስቆ መንገድ ላይ ሳውልን እንደተገናኘው በድንቅ ይገናኝና ሕዝቡን ከመከላከልም አልፎ የእነዚያን አሳዳጆች ሕይወት በመለኮታዊ አሰራሩ ለውጦ ለራሱ ክብር ይጠቀምባቸዋል።ይህ በዘመናት መሃል ታሪክን የመስራት ልማዱ ዛሬም የሚሰራና ወደ ፊትም የሚቀጥል መሆኑን ተረድተን ፀንተን ኃይማኖታችንን በመጠበቅና የሚደርስብንን መከራ ሁሉ እየታገስን እስከ ፍፃሜው ድረስ በታማኝነት እንድናገለግለው የጌታ መልካም ፈቃድ ነው።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"…ይህ በአሕዛብም፥በነገሥታትም፥ በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና፤" ሐዋ 9፥15

# ጥናት 17: ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም

የምንባብ ክፍል ሐዋ 9፣ 20-31

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በእስጢፋኖስ ተወግሮ መሞት የተባበረውንና ቤተ ክርስቲያንን እያሳደደ ብዙ ክርስቲያን ወገኖችን ወደ ወኅኒ ያስገባ የነበረውን ኃይለኛ የነበረውን ሳውል የተባለውን ሰው ጌታ እንዴት እንደተገናኘውና ሕይወቱንም እንደለወጠው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ይህ በአስደናቂ መንገድ ጌታ የተገናኘውና ሕይወቱን የለወጠለት ሳውል ከደማስቆ ቅዱሳን ጋር ኅብረት ማድረጉና በየሥፍራው ሁሉ እየተዘዋወረ የክርስቶስን አዳኝነት ለሌሎች በመመስከሩ ምክንያት እርሱም በተራው ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል መጀመሩን እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሳውል በደማስቆ ካነበሩት ደቀ ማዛሙርት ጋር ለጥቂት ቀናት ከኖረ በኋላ ወዲያው ማድረግ የጀመረው ምንድር ነው?
2. ስለ ክርስቶስ ሲሰብክ ሳውል የሰሙት ሁሉ በመገረም የተባባሉት ምን ነበር?
3. አይሁድ ሳውልን ሊገሉት የፈለጉበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ሳውልን ለመግደል ያደረጉት ሙከራስ ምን ነበር? (ከቁ23-24)
4. ደቀ መዛሙርቱስ ሳውልን ከአይሁድ ግድያ ለማስመለጥ ያደረጉት ነገር ምን ነበር? (ቁ25)
5. ሳውል በኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሊተባበር በሞከረ ጊዜ ከነርሱ በኩል የገጠመው ምላሽ ምን አይነት? በርናባስስ ምን አደረገለት? (ከቁ26-27)
6. ሳውል በኢየሩሳሌም ቆይታው ምን ያደርግ ነበር? ከግርክ የመጡት አይሁዶችስ ምን ሊያደርጉበት ፈለጉ? (ከቁ28-29)
7. ወንድሞች ይህን ባወቁ ጊዜ ሳውልን ከአይሁድ ግድያ ለማስመለጥ ከኢየሩሳሌም ወዴት ሰደዱት? (ቁ30)
8. በሳውል መለወጥና የወንጌል አገልግሎት መጀመር ጋር ተያይዞ በይሁዳ ሁሉ፤በገሊላና በሰማርያ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሆነው መልካም ነገር ምን ምን እንደነበረ ዘርዝሩ።(ቁ31)

ሕይወት ጋር ማዛመድ

9. ዛሬስ ኃይለኛ የሚባሉ የወንጌል ተቃሚዋሚዎችን ጌታ በድንቅ በመገናኘት ሕወታቸውን ለውጦ ለክብሩ እንደሚጠቀምባቸው ምን ያህል ታምናለህ/ሽ?
10. አንተስ /ቺስ ልክ እንደ ሳውል ስለ ክርስቶስ በየሄድክበት/ሽበት ሁሉ ምን ያህል ትናገራለህ/ሽ?
11. ትናንት ወዳጆች በነበሩ ሰዎች በክርስቶስ ምክንያት ዛሬ ብትሰደድ ምን ያህል ለመቀበል ተዘጋጅተሃል/ሻል?

ማጠቃለያ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ በየዘመናቱ በቤተ ክርስቲያናን ላይ በተቃውሞ የሚነሱትን አሳዳጆች በኃያል ክንዱ በአስደናቂ ሁኔታ በማንበርከክ እንዲታዘዙት አድርጎ በቀረላቸው ዘመን ሁሉ ለስሙ ክብር እንዲኖሩለትና እንዲሮጡለት የሚያደርግ መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ አሳዳጅ ከነበረው ከሳውል ሕይወት ለእኛም ብዙ መንፈሳዊ ትምህርት ይቀርልናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“.... አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ፤ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።” ሐዋ 9፣31

## ጥናት 18: የጴጥሮስ አገልግሎት በልዳን የኢዮጴ

የምንባብ ክፍል ሐዋ 9፣ 32-43

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በአስደናቂ መንገድ ጌታ የተገናኘውና ሕይወቱን የለወጠለት ሳውል ከደማስቆ ቅዱሳን ጋር ኅብረት ማድረጉና በየሥፍራው ሁሉ እየተዘዋወረ የክርስቶስን አዳኝነት ለሌሎች በመመስከሩ ምክንያት እርሱም በተራው ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል መጀመሩን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔር በጴጥሮስ አገልግሎት ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዲሉና የስጋና የነፍስ መዳን እንዲሆንላቸው እያደረገ ይህም የመንፈስ ቅዱስ ስራ ለወንጌል መስፋፋትና ለቤተ ክርስቲያን እድገት ምክንያት ሲሆን እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጴጥሮስ ወደ በልዳ የሄደው ለምን ነበር?
2. የበልዳው ኤንያ የተባለ ሰው ሕመም ምን ነበር?
3. የኤንያ ፈውስ በምን አይነት መንገድ ተከናወነ? መፈወሱን ያዩ ሰዎችስ ምን አደረጉ?
4. ጣቢታ/ዶርቃ/ የተባለችዋ ደቀ መዝሙር በኢዮጴ አካባቢ በምን አይነት የአኗኗር ስነ ምግባር የምትታወቅ ሴት ነበረች?
5. ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስን ቶሎ እንዲመጣ የፈለጉበት ምክንያት ምን ነበር? (ቁ38-39)
6. ዶርቃ ከሞት እንድትነሳ የጌታ አገልጋይ የሆነው ጴጥሮስ ያደረገው ነገር ምን ነበር? (ቁ39-41)
7. እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን ወይም ከጠራቸው ጋር አብሮ መስራት ውጤቱ ምን ይመስልሃል? (ቁ35 ና 41)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

8. ካለፈው ጥናትና ከዛሬውም እንደተመከትነው በስደት መካከል የእግዚአኣብሔር ጣልቃ ገብነት በሕዝቡ ስለሚያመጣው ውጤት የምታውቁት የሕይወት ልምምድ ወይም ምስክርነት ካለ አካፍሉ።
9. ደግነትና ለጋስነት በሰዎች ሕይወት ሊፈጥር ስለ ሚችለው መልካም ተጽዕኖ ከዚህ ክፍል እኛስ ምን ማድረግ እንደሚገባን ያስምተረናል? ውሳኔያችንስ ምንድር ነው?
10. ለወንጌል መስፋፋት ስደት የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ ቢኖረውም የፈውስ ጸጋ በሙላት መታየትና ለጋስነት/ለችግረኞች ቸርነትን ማድረግ ያላቸው ሚና ምን ያህል ይመስልሃል?

ማጠቃለያ

ለቤተ ክርስቲያን እድገትና ለወንጌል መስፋፋት ከውጪ የሚመጣ ስደት፥ የመፈስ ቅዱስ ስጦታ በስራ ላይ መዋል እና እኛም ያለንን ለሌሎች ማካፈል መቻላችን ምን ያህል ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ከክፍሉ ተመልክተናል።በመሆኑም ሁላችንም የሚጠበቅብንን ድርሻ ሳንታክት ለመወጣት እንድንችል ከልብ ውሳኔ በማድረግ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሙላት እንዲሰራ አጥብቀን መጸለይ ይ ይገባናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"…እርስዋም መልካም ነገር የሞላባት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች።" ሐዋ 9፣36

# ጥናት 19: የቆርኔሌዎስና የጴጥሮስ ራእይ

የምንባብ ክፍል ሐዋ 10፣ 1-22

መግቢያ

ባለፈው ጥናት እግዚአብሔር በጴጥሮስ አገልግሎት ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዲሉና የስጋና የነፍስ መዳን እንዲሆንላቸው እያደረገ ይህም የመንፈስ ቅዱስ ስራ ለወንጌል መስፋፋትና ለቤተክርስቲያን እድገት ምክንያት ሲሆን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ቆርኔሌዎስ በቤቱ ሆኖ ጴጥሮስም በሌላ ስፍራ በእንግድነት ባረፈበት ቤት ሲጸልይ ሳለ በራእይ የእግዚአብሔርን ድምፅ በየግላቸው መስማታቸውንና ባዩትም ራዕይ የእግዚአብሔር ሰዎችን የማዳን መለኮታዊ ቅንብር በጴጥሮስ ታዛዥነት የአህዛብ ወገን ወደ ሆነው ወደ ቆርኔሌዎስ ወንጌል እንዴት እንደገባ እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 1 እና 2 እንደምንመለከተው ስለ ቆርኔሌዎስ ማንነት ማለትም ስለ ስራው፣ ስለ ኑሮው ደረጃ እና ስለ አምልኮው የተገለጸው ነገር ምንድን ነው?
2. እግዚአብሔር ለቆርኔሌዎስ መልአኩን ሲልክለት ስለ ጸሎቱ መልስ ምን ተናገረው? ምንስ እንዲያደርግ አዘዘው?
3. ቆርኔሌዎስ መልአኩ እንደለው ያደረገው ነገር ምን ነበር? (ቁ 7 እና 8)
4. ጴጥሮስስ ያየው ራዕይ ምን ነበር? ቆርኔሌዎስ ካየው ጋር በምን ይለያል?
5. ጴጥሮስስ ከራዕዩ በኋላ ለሰማው ድምጽ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? (ቁ13-16)
6. በቁ13 እና 15 ላይ ጴጥሮስ ድምጽ እንደሰማ ሲናገር በቁጥር 19 ላይ ደግሞ መንፈስ ሰዎች እንደሚፈልጉት ሲናገረው እናያለን? ጴጥሮስ በራዕዩ በተደጋጋሚ ያየው የመልዕክቱ ዋና ፍሬ ሀሳብ ምን ነበር?
7. ከዚህ ሁሉ በኋላ የሆነው ነገር ምን ነበር? ጴጥሮስስ ስላየው ራዕይና ስለ ሰማው ድምፅ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች እርሱ ወደ ነበረበት ቤት ሲደርሱ ምን አደረገ? ሁኔታውን በዝርዝር ተነጋገሩበት። (ቁ 19-22)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

8. ዛሬም እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ላንተም የሚናገር አምላክ እንደሆነ አውቀህ/ሽ ሁል ጊዜ ድምጹን ለመስማት ምን ያህል ዝግጁ ነህ /ሽ?
9. የምስራቹ ወንጌል ማንንም ወገን ሳይለይ ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ መሆኑን አውቀህ እግዚአብሔር ደህንነትን ላዘጋጀላቸውና አንተ ለምታገኛቸው ሰዎች ወንጌልን ምን ያህል ትናገራለህ/ሽ?

ማጠቃለያ

የወንጌልን መልዕክት ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲድኑንበት የማድረስ ሀላፊነት ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታናል። በመሆኑም ወንጌልን መናገር ያለብን ለእኛ በመሰለን መልኩ ብቻ ሰው መርጠን ሳይሆን ለሰው ሁሉ መልዕክተኞችና አስታራቂዎች እንድንሆን የተጠራን መሆናችንን አውቀን ጌታ በሚልከን ሥፍራ ሁሉ ታዛዥ መልዕክተኞቹ ልንሆንለት ይገባናል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ልዩነት የለምና አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ፣ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው፣” ሮሜ 12፡10

# ጥናት 20: ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት

የምንባብ ክፍል ሐዋ 10፣ 23-48

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ቆርኔሌዎስ በቤቱ ሆኖ ጴጥሮስም በሌላ ስፍራ ሆኖ በእንግድነት ባረፈበት ቤት ሲጸልይ ሳለ በራእይ የእግዚአብሔርን ድምፅ በየግላቸው መስማታቸውንና ባዩትም ራዕይ የእግዚአብሔር ሰዎችን የማዳን መለኮታዊ ቅንብር በጴጥሮስ ታዛዥነት የአህዛብ ወገን ወደ ሆነው ወደ ቆርኔሌዎስ ወንጌል እንዴት እንደገባ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች የፈጸመውን /ያደርገውን ማዳን በዝርዝር እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 25 ቆርኔሌዎስ ከጴጥሮስ ጋር በተገናኙበት ወቅት ለጴጥሮስ ምን ሲያደርግ እንመለከታለን? ጴጥሮስስ ለዚህ የቆርኔሌዎስ ድርጊት ምን ምላሽ ሰጠ?
2. በቁ35 ላይ እንደምንመለከተው "እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ .........በእውነት አስተዋልሁ። "ከሚለው አነጋገር ጴጥሮስ እስከዚህች ሰዓት ድረስ አቋሙ ምን ዓይነት ነበር? (ይህ አቋሙ የተቀየረው እንዴትና መቼ እነደነበር አስታውሱ ።)
3. ስለ ጌታ ኢየሱስ "ምስክሮች" ነን ብሎ ጴጥሮስ የጠቀሳቸውን ነጥቦች ምን ምን እንደሆኑ ከቁ35 -43 ባለው በዝርዝር ለመዳሰስ ሞክሩ።
4. ጴጥሮስ ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ የተፈጸመው ምን ነበር? ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ከተገረዙት ወገን የሆኑት አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ማረጋገጫ በልሳኖች ሲናገሩ ሲያዩ ምን አሉ?
5. በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ "በኢየሱስ ስም" እንዲጠመቁ ማድረጉ ጌታ አደራ የሰጠውን የታላቁን ተልዕኮ ትዕዛዝ የፈጸመ ይመስልሃል? እንዴት? (ከማቴ 28:19-20 ጋር በማንበብ ያነፃፅሩ)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. ሁላችን እንደ ቆርኔሌዎስ ከአሕዛብ ወገን ሆነን ሳለን የእግዚአብሔር ምሕረት ለእኛም ተገልጦ መዳናችን ምን ያህል ያስደስተናል? ይህ ምህረቱ ለሌሎችም ገና እንደሚቀጥል ተረድተን እንደ ጴጥሮስ ለጌታ ድምጽ በመታዘዝ ወዳልዳኑ ሰዎች ሄደን ስለ ጌታ አዳኝነት ምን ያህል እንናገራለን? ካልሆነስ የማንናገርበት ምክንያቱ ለምን ይመስልሃል?
7. ጌታን ለማያዉቁ ወንጌልን ስንመሰክር በሰዎች የግል ሕይወት ዙሪያ ብዙ ከማውጠንጠን ወይም በአንድ ጥቅስ ትርጉም አሰጣጥ ላይ ከመከራከር ይልቅ የመልዕክታችን ዋና ትኩረት በጌታ ኢየሱስ አዳኝነት ላይ ሲሆን እጅግ ውጤታማ መሆኑን ከክፍሉ ምን ያህል ተረድተሃል?
8. በዚህ ዘመን በአንዳንድ የኃይማኖት ተቋማት ለሰው በተለይም ለጌታ ታማኝ በሆኑ አገልጋይ ባሮች ስም **የአክብሮት ስግደት** መሰጠቱ በክፍሉ ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ከሰጠው ምላሽ አንፃር አንዴት ትመዝነዋለህ/ሽ?

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር እርሱን በእውነት የሚፈራውንና ከልቡ የሚፈልገውን ሰው አይሁድ ይሁን አህዛብ ለማንም ፊት ሳያደላ እኩል እንደሚወድና ድምጹን ሰምተው ለሚታዘዙት ሁሉ የድነትን መንገድ እንደሚገልጥላት ምን ጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ነው።ለዚህም ሰው ሳይሆን እርሱ ራሱ ያዘጋጀው ሌላ አማራጭ የሌለው ለሰው ልጆች ሁሉ ሕይወት መዳኛ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን እንረዳለን።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ፥ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልሁ ።" ሐዋ 10፤35

## ጥናት 21: ጴጥሮስ አህዛብ ቤት ለምን እንደገባ አስረዳ

የምንባብ ክፍል ሐዋ 11፣ 1-18

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ጴጥሮስ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ወደ የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ቤት ሄዶ ወንጌልን በመስበኩ ለራሱና ለቤቱ ሰዎች እንዲሁም ተሰብስበው ቃሉን ለሰሙት መዳን እንደሆነላቸው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የጴጥሮስ ወደ አሕዛብ ቤት መግባት ጥያቄ ለሆነባቸው ከአይሁድ ወገን ለሆኑት አማኞች ወደ አሕዛብ ቤት የገባበትን ምክንያት እንዳስረዳቸው እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሐዋርያትና በይሁዳ የነበሩት ወንድሞች የሰሙት ዜና አሕዛብ ምን መሆናቸውን የሚገልጽ ነበር?
2. ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ ከተገረዙት ወገን የሆኑት ጴጥሮስን የተከራከሩበት መንቀፊያ ነጥብ ምን ነበር?
3. ከቁ4-10 ጴጥሮስ ለተከራካሪዎቹ ያስረዳቸው ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ያየው ራእይ ትርጉም ምን ይመስልሃል?
4. በዚያው ሰዓት ጴጥሮስን እንሂድ ለማለት የመጡት ሦስቱ የቂሳርያ ሰዎች ማን ልኳቸው ነበር? መንፈስ ቅዱስስ ጴጥሮስን ምን ያደርግ ዘንድ ነገረው?
5. ከጴጥሮስ ጋር አብረውት ወደ ሰውየው ቤት የሄዱት ስድስት ወንድሞች ከየት የመጡ ነበሩ (ሐዋ ቁ 10:24ን ይመልከቱ።) ጴጥሮስ ሰውዬው እያለ የሚጠቅሰው ሰውስ ማንን ነው?
6. ለሰውየው በራእይ መልአኩ የነገረው የጴጥሮስ ወደ ቤቱ መምጣት ለሰውየውና ለቤቱ ምን ሊሆኑ የሚችሉበትን ነገር ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ነበር?
7. በተገረዙት /አይሁድ ላይ የወረደው መንፈስ ቅዱስ ላልተገረዙት/አህዛብም መውረዱ ሰዎች ይህን ከእግዚአብሔር እንዲቀበሉ ማሟላት ያለባቸው ምንድር ነው? (ሐዋ 11:17ን ከገላ3:28ና ከቆላ3:11 ጋር ያነፃፅሩ ።)
8. አሕዛብ ቤት በመግባቱ ጴጥሮስን የተከራከሩት ያቀረበላቸውን እውነታ ሲሰሙ ምን አሉ? ምንስ አደረጉ?

ሕይወት ጋር ማዛመድ

9. አማኞች ሁሉ እኩል የጌታ ልጆች ሆነው ሳለ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ወገኖች ከመንፈሳዊና ማህበራዊ ህብረት የሚያገሉበት ጉዳይ አስተውለህ ታውቃለህ? የአንተስ አመለካከት ከዚህ ምን ያህል የፀዳ ነው?
10. ሰዎች የእኛን ሁኔታ ምንም ሳይገነዘቡ ከራሳቸው የተሳሳተ አመለካከት ብቻ በመነሳት ቢከራከሩን እንደ ጴጥሮስ በሰከነ መንገድ ጉዳያችንን በማስረዳት በከንቱ ከመንቀፍ እንዲቆጠቡና እግዚአብሔርንም እንዲያመሰግኑት ምን ያህል ልበ ሰፊዎች ነን?
11. መንፈስ ቅዱስን ሰምቶ ስጋዊ አመለካከታችንን በማሸነፍ እንደ ጴጥሮስ ለሰዎች መዳን ስንል ምን ያህ የመታዘዝ እርምጃ እንወስዳለን?

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን የሚጠቀምበት መለኮታዊ ቅንብር ምን ያህል ረቂቅ እንደሆነ ጴጥሮስ መጀመሪያ ይዞት የነበረውን የተሳሳተ አመለካካት መጣሉና ያንን አሕዛብ ሰውም ለደህንነት ማዘጋጀቱ ጌታ እንደተናገረውም ለዛ ቤት መዳን መሆኑ እኛም እንደዚሁ ከአህዛብ ወገን ሆነን ሳለ በእግዚአብሔር ምሕረትን አግኝተን ለመዳናችን ቋሚ ምስክሮች ነን።በመሆኑም ያኔ የተጀመረው ይህ የጌታ ማዳን እኛ ላይ የሚያበቃ ሳይሆን ከእንድግዲህም በኋላ በእኛ ለቃሉ ታዛዥነት ብዙ የሚድኑ ሰዎችን ጌታ እነደሚያዘጋጅ ተረድተን በምንሄድበት ሁሉ ተልዕኮአችንን ልንፈጽም ይገባል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

“እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ከሰማይ መለሰልኝ ።” ሐዋ 11፣9

## ጥናት 22: የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን

የምንባብ ክፍል ሐዋ 11፣ 19-30

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ደግሞ የጴጥሮስ ወደ አሕዛብ ቤት መግባት ጥያቄ ለሆነባቸው ከአይሁድ ወገን ለሆኑት አማኞች ወደ አሕዛብ ቤት የገባበትን ምክንያት እንዳስረዳቸው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእስጢፋኖስ መከራ ምክንያት የተበተኑ ምዕመናን እስከ አንፆኪያ ድረስ ቃሉን መስበካቸውን ሰምተው ከኢየሩሳሌም በርናባስን ወደ አንፆኪያ እንደላኩላቸው እናያለን ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የተበተኑት ምዕመናን ቃሉን የሰበኩት በየትኞቹ ከተሞች ነበር? ለግሪክ ሰዎችስ ወንጌልን የሰበኩት የየትኞቹ ከተሞች ሰዎች ነበሩ?
2. በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወሬውን ስትሰማ ምን አደረገች? በአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያንስ በርናባስን ደስ ያሰኘው ምን ነበር?
3. በርናባስ ምን ዓይነት ሰው ነበር? ጳውሎስን ፈልጎ በጠርሴስ ካገኘው በኋላ ወደ አንፆኪያ ያመጣውስ ለምን ነበር?
4. ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩበት ስፍራ የት ነው? **ክርስቲያን** የሚለው የቃሉ ትርጉምስ ምን ማለት ይመስልሃል?
5. የአጋቦስን ትንቢት ትክክለኛነት ወይም እውነተኛነት እንዴት ማወቅ ወይም በምን ዓይነት ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. በስደትና መከራ የተበተኑት የኢየሩሳሌም ምዕመናን ይህንን መጥፎ የሚመስል አጋጣሚ በየደረሱበት ሁሉ ቃሉን እየሰበኩ ወንጌልን ለማስፋፋት ይበልጥ እንደ ምቹ እድል እንደሆነላቸው ስንመለከት በዚህ ዘመንና ሃገር ለምንገኝ ለእኛ ምን ሊያስተምረን ይችላል?
7. በርናባስ ዻውሎስን ፈልጎ ወደ አንፆኪያ ከማምጣቱስ አንፃር ምን የምንማረው ነገር ሊኖር ይችላል?
8. በዚህ ዘመን ባለችዋ ቤተ ክርስቲያን ነብያት ተብለው የሚጠሩ ሰዎችንና የትንቢቶቻቸውን ትክክለኛነት ወይም እውነተኛነት ይዘት በተረዳችሁት የእግዚአብሔር ቃል መሰረት እንዴት ትመዝኑታላችሁ?
9. በመካከላችሁም ሆነ በአካባቢያችሁ የእናንተ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቢኖሩ የምንችለውን ተግባራዊ እርዳታ ለማድረግ ምን ያህል ፈቃደኞች ነን? ከሆነን ደግሞ ብዙ ጊዜ ሳንፈጅ ለምን ዛሬውኑ አንጀምርም? ("ችግር ጊዜ አይሰጥምና")

ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ልጆች በየትኛውም ዓይነት ምክንያት ከትውልድና ከመኖሪያ ስፍራቸው ተሰደው ወደ ተለያዩ ሀገሮች ቢበተኑ ያንን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የጌታን ቃል በመስበክ በየደረሱበት የዓለም ዳርቻ ሁሉ መንግስቱን እንዲያሰፉ ጌታ የሰጣቸውን የወንጌል አደራ በታማኝነት ሊወጡ ይገባል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፥ቁጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘውር አሉ።" ሐዋ 11:21

## ጥናት 23: "የያዕቆብ መሰዋትና የጴጥሮስ ከእስር መውጣት

የምንባብ ክፍል፤ ሐዋ 12: 1-19

መግቢያ

ባለፈው ጥናት በእስጢፋኖስ መከራ ምክንያት የተበተኑ ምዕመናን እስከ አንፆኪያ ድረስ ቃሉን መስበካቸውን ሰምተው ከኢየሩሳሌም በርናባስን ወደ አንፆኪያ እንደላኩላቸውና በዚያም መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰራው ትልቅ ስራ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እየተቀጣጠለ የነበረውን የወንጌል ኀይል ሊያዳክም የተናሳውን የሄሮድስን ሤራና በቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ይደረግ በነበረው ጥብቅ የጸሎት ኀይል እግዚአብሔር ጴጥሮስን በታምር እንዴት ከእስር ቤት እንዳስወጣው እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሄሮድስ በክርስቲያኖች ላይ እያደረገ የነበረው ምን ነበር? ድርጊቱስ በአይሁድ ላይ የፈጠረው ምን ነበር? (ከቁ1-3 መከራው በቅዱሳን ዘንድ የፈጠረው ሁኔታ ምን እንደ ነበረ አብራራ። (አንድነት፣ ጸሎት፣ ሀይል)
2. በወቅቱ የነበረውን የጴጥሮስን የእስራት ጥንካሬና ጣልቃ የገባውን የእግዚአብሔር የማዳን ኃይል ተወያዩ።
3. በጽኑ እስራት የነበረው ጴጥሮስ የነበረውን ጠቅላላ ስሜት እንዴት ትረዳዋለህ?
4. የጌታ መልዓክ በዚያች ሌሊት በየደረጃው ያደረገው ምን ነበር?
5. በምዕራፉ ውስጥ በያዕቆብና በጴጥሮስ አገልግሎት ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማና ፈቃድ እንዴት ትረዱታላችሁ?
6. ጴጥሮስ በጠንካራ ጥበቃ ታሥሮ በነበረበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን የወሰደችው እርምጃ ምን ነበር? (ቁ5)
7. 'አጥብቆ' የሚለው ቃል ስለ ጸሎት ምንነት ምን እንደሚያስረዳ ተወያዩ ።

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

8. ዛሬም በዘመናችን ወንጌል የሚያስከፍለው ዋጋ ምን እንደሆነ ተወያዩ።ከግል ሕይወትህ ጋር ያለውን ቀተጥኛ ተዛምዶ(ምስክርነት) ካለ ለቡድኑ አካፍል።
9. ጸሎት በወንጌል ስራ ላይ ስላለው ሚና ከክፍሉ ምን እንማራለን? የተጸለየበትን ጉዳይ እግዚአብሔርን በእምነት ስለመጠበቅና ሲፈጸም ደግሞ ስለ መቀበል ከክፍሉ ምን እንማራለን?

ማጠቃለያ

ከዛሬው ጥናታችን በወንጌል አገልጋዮች ላይ በየዘመኑ ጠላት ዲያብሎስ የሚዘረጋውን ወጥመድ ለማፍረስ የቤተ ክርስቲያን የአንድነትና የእምነት ጸሎት እግዚአብሔር አምላክ እንደሚሰማና ሴራውንም እንደሚያከሽፍ ስንመለከት የቤተ ክርስቲያን ጥብቅ ጸሎት በወንጌል ስራ ላይ ስለ ሚያበረክተው ትልቅ ሚና እንረዳለን።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር ።" ሐዋ 12:5

## ጥናት 24: የሄሮድስ አሟሟት

የምንባብ ክፍል፤ሐዋ 12: 20-25

መግቢያ

ባለፈው ጥናት እየተቀጣጠለ የነበረውን የወንጌል ኀይል ሊያዳክም የተናሳውን የሄሮድስን ሤራና በቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ይደረግ በነበረው ጥብቅ የጸሎት ኀይል እግዚአብሔር ጴጥሮስን በታምር እንዴት ከእስር ቤት እንዳስወጣው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በዚያን በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ መከራና ጫና ከማምጣትም አልፎ የወንጌል መልዕክተኛ የነበረውን ሐዋርያው ያዕቆብን አሰይፎ በማስገደልና ጴጥሮስንም ወደ ወኅኒ በማስጣል ቅዱሳንን እጅግ ያስጨንቅ የነበረው የንጉስ ሄሮድስን የውርደት አሟሟት እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የጢሮስና የሲዶና ሰዎች እርቅ የለመኑበት ምክንያትና የንጉሡ ምላሽ ምን ነበር?
2. እግዚአብሔርን ያስቆጣውና ንጉሱን ለሞት ያበቃው ምን እንደነበር ተወያዩ።
3. የንጉሱን የአሟሟት ሁኔታ ልዩና አስገራሚ የሚያደርገው ምንድር ነው?
4. ይህ በእግዚአብሔር ቃል መስፋፋት ላይ ያለው አዎናዊ ተጽዕኖ ምንድር ነው ትላለህ?
5. የጴጥሮስ መፈታት፣ የተቃዋሚው ንጉሥ መሞትና ለወንጌሉ ስራ ተሰማርተው የነበሩት ባርናባስና ሳውል አገልግሎታቸውን ፈጽመው መመለሳቸው በቃሉ ዕድገት ምን የፈጠረ ይመስልሃል?
6. በዙሪያው ባሉ አማኞች ዘንድ ይፈጠራል የምትሉትን የጊዜውን ድባብ ተወያዩ።

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. ከዚህ ክፍል ስለ ወንጌልና ስለ ወንጌል መልዕክተኞች እንዲሁም የወንጌል ዋነኛ ባለቤት ስለሆነው ስለ እግዚአብሔርና ስለ እግዚአብሔር ክብር ምን እንማራለን?
8. የዛሬውን ጥናት ከዙሪያችንና ከዓለም ሁኔታ ጋር በማዛመድ በዚህ ዘመን ለምንገኝ ለእኛ የሚያስተላልፈውን መልዕክትና ከክፍሉ ምን እንደቀረላችሁ ተወያዩ።

ማጠቃለያ

ቅዱሳን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመርተው በሚያደርጉት ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ውጤቱ ብዙ ነፍሳትን አድኖ ወደ ቤቱ በመጨመር የእግዚአብሔርን መንግስት የሚያሰፋና የጨለማውን ግዛት የሚንድ መሆኑ እውነትና የጌታ አጀንዳም ነው።በአንጻሩ ደግሞ መንግስቱ የተነቃነቀበት ዲያብሎስ በቁጭትና በበቀል በእግዚአብሔር አገልጋዮች ላይ የሚችለውን አስከፊ ነገር ሁሉ በሕይወታቸው ከማድረግ የቦዘነበት ጊዜ አለመኖሩ ግልጽ ነው። በየዘመኑም የሚነሱ ነጋስታትን እንደ ዋና የማጥቂያ መሳሪያ አድርጎ ሲጠቀም ከብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና እኛም በዘመናችን ካየነው ተጨባጭ ድርጊቶች መናገር እንችላለን።በዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔርና ህዝቡ በጠላት ላይ በአሸናፊነት እስካዛሬ ዘልቀዋል ወደፊትም ድሉ የእግዚአብሔርና የህዝቡ ሆኖ ይቀጥላል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"የእግዚአብሔር ቃል ግን ያድግና ይበዛ ነበር።" ሐዋ 12:24

## ጥናት 25: የባርናባስና ሳውል (ጳውሎስ)መላክ

የምንባብ ክፍል፤ሐዋ 13: 1-12

መግቢያ

ባለፈው ጥናት ደግሞ በዚያን በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ መከራና ጫና ከማምጣትም አልፎ የወንጌል መልዕክተኛ የነበረውን ሐዋርያው ያዕቆብን አሰይፎ በማስገደልና ጴጥሮስንም ወደ ወኅኒ በማስጣል ቅዱሳንን እጅግ ያስጨንቅ የነበረውን የንጉስ ሄሮድስን የውርደት አሟሟት ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለስራው እንዴት እንደሚለይና አብሮአቸው እንዴት እንደሚሰራ ከበርናባስና ከሳውል/ጳውሎስ/ ለአገልግሎት መለየት ጋር አያይዘን በዝርዝር እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎትና አመራር ላይ የነበረው ስብጥር ምን ይመስል ነበር? (ቁ 1.)
2. መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕዝቡ ያመጣው መልዕክትና እነርሱ ደግሞ የወሰዱት እርምጃ ምን ነበር? (ከቁ 2-3)
3. መንፈስ ቅዱስ ለአገልጋዮቹና ለህዝቡ በርናባስንና ሳውልን ምን እንዲያደርጉለት ተናገረ?
4. ለወንጌል አገልግሎት ስለ መላክ ጉዳይ ሚና ምንድር ነው? የቤተ ክርስቲያን ድርሻስ ምንድር ነው?
5. በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከለዩዋቸውና ከጸለዩላቸው በኋላ በርናባስና ጳውሎስት ለወንጌል ስራ የተላኩት ወዴት ነበር?
6. በርናባስንና ሳውልን በሄዱበት ስፍራ የወንጌል ሥራው ያጋጠመው ተግዳሮት ምን ይነበር?
7. የአገረ ገዥው የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰማ መፈለግ ሲመለከት ጠንቋዩ ምን አደረገ? ጳውሎስ ያደረገውስ ምንድርን ነው? (ከቁ7-11)
8. የተደረገው ተአምራት በአገረ ገዥው ላይ ምን ፈጠረ? (ቁ 12)

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

9. ይህ ክፍል ከመንፈስ ቅዱስና ከሌሎች ቅዱሳን ጋር አብሮና ተባብሮ ስለ መሥራት ምን ያስተምረናል?
10. በዙሪያችሁና በቤተ ክርስቲያን ባለው የወንጌል ስራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን ድርሻ ከተወያያችሁ በኋላ በምትደርሱበት የጋራ ምላሽ ላይ በጋራ ጸልዩ።

ማጠቃለያ

አግዚአብሔር አምላክ ገና ከጥንት ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ ነብያትን ፤ህዝቡን የሚመሩለትንና የሚያስተምሩትን እንዲሁም ወንጌል እየሰበኩ በየስፍራው ቤተ ክርስቲያንን የሚተክሉትን አገልጋዮች በልዩ መንገድ ሲጠራና ሕዝቡን ደግሞ በመለየት ስራው ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር እንዲተባበርና የተለዩትንም አገልጋዮች ለተጠሩበት የወንጌል ሥራ እንዲያሰማራ ድርሻን ሰጥቷል።የወንጌል ስራ በዚህ መልኩ እንደ ዱላ ቅብብል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ዛሬ እኛ ጋ ደርሷል። በመሆኑም የዚህ ዘመኗም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ይህንን አገልጋዮችን የመለየትና እግዚአብሔር ለጠራቸው ስራ የማሰማራት ድርሻዋን ወደፊት ስለሚድነው ትውልድ በማሰብ ማስቀጠል ይገባታል።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

> “እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።”
> ሐዋ 13:2

# ጥናት 26: የበርናባስና የጳውሎስ አገልግሎት በጲስድያ

የምንባብ ክፍል፤ሐዋ 13:13-32

መግቢያ

ባለፈው ጥናት መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለስራው እንዴት እንደሚለይና አብሮአቸው እንደሚሰራ ከበርናባስና ከሳውል/ጳውሎስ/ ለአገልግሎት መለየት ጋር አያይዘን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በርናባስና ጳውሎስ በጲስድያ ወዳለች አናጾኪያ ሄደው በምኩራብ እግዚአብሔር በገባው ቃል መሰረት አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን እንደገለጠና ጽድቅና የሀጢያት ይቅርታም የሚገኘው እርሱን በማመን መሆኑን ሲመሰክሩላቸው እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በርናባስና ጳውሎስ ከቆድሮስ ደሴት ተነስተው በጲስድያ ወዳለችው ሌላዋ አንጾኪያ ሲሄዱ ምን አደረጉ? የተከፈተላቸውስ አገልግሎት ምን ነበር? (ቁ13 – 15)
2. ጳውሎስ በሙክራብ ለተሰበሰበው ህዝብ ሲናገር እግዚአብሔር በግብጽ ህዝቡን እንደታደገውና በበረሀ እየመራ ከነዓንን በብርቱ ሰልፍ እንዴት እንደሰጣቸው የተነተነው ምን እንዲያስተውሉ ፈልጎ ይመስልሀል/ሻል? (ቁ15 – 20)
3. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የገባውን ቃል ኪዳን ሊፈጽም የመረጠውን ሰው "እንደ ልቤ የሆነ" እያለ ሲመሰክርለት፣ የእግዚያብሄርን ቃል ታዛዥ ስለ መሆኑ በምን ስለ ተገለጠ ይምስልሃል/ሻል? (ቁ20 – 23)
4. ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የሰጠው ምስክርነት ምን ነበር? የንስሀ ጥሪውን ለተቀበሉ ሰዎች ይህ መልዕክት ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስልሀል/ሻል? (ቁ24 – 25)
5. ኢየሱስን ለሞት የሚያደርሰው አንዳች ምክንያት ሳይኖር መሰቀሉና መሞቱ እንዲሁም ደግም ከሞት መነሳቱና ለብዙ ምስክሮች መታየቱን ጳውሎስ መግለጹ ለሰዎች መዳን የትንሳኤው ምስክርነት ምን ያህል ጠቃሚ ይመስልሀል/ሻል?
6. "…አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ…" ተብሎ የተጻፈው ቃል ስለ ኢየሱስ ምንን የሚገልጽ ነው? (ቁ33)

ሕይወት ጋር ማዛመድ

7. ጳውሎስና በርናባስ በምኩራብ ስብከታቸውን ያመኑትን ወገኖች በእግዚአብሔር ጸጋ ጸንተው እንዲቆዩ እንደ መከሩዋቸው ዛሬም ጌታ በቃሉ ወደ ቤቱ የሚያመጣቸውን በመንከባከብና በመምከር የምናሳየው ትጋት እስከምን ድረስ ሊሆን ይገባል ትላለህ/?
8. አይሁድ በየሰንበቱ የሚነበበውን የነብያት ድምጽን ሳያስተውሉ በቅንዓት እየተሳደቡ የኢየሱስን አዳኝነት እንዳይሰበክ መቃወማቸውን ስታይ ከሀይማኖተኝነት የሆነ ግብዝነትና በእምነት መኖር ያላቸውን ልዩነት የሚገልጽ የህይወት ምስክርነት ካለ አካፍል/ዪ ።

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር አብ ከዘመናት በፊት በነቢያት የተናገረው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የፈጸመው ታላቅ የደህንነት ስራ ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ የብዙዎችን ልብ በፍቅር ማርኳል። በዚህ ጥናት እንዳየነው ባለንበት ከተማና መንደር ሁሉ ተግዳሮቶችን ሁሉ እየተቋቋምን ቃሉን በሙውደድ ፣ በመታዘዝ እና በመመስከር ብንኖር የብዙዎችን ልብ የሚማርክ የእውነት ቃል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም እስከ ለዘለ ዓለምም ጌታ ነው።

በቃል የሚጠና ጥቅስ

"እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምስራቹን ለእናንተ እንሰብካን፤" ሐዋ 13፣ 32